በዶ/ር ኢዮብ ማሞ የተጻፉ መጻሕፍት



“አመራር A to Z”፡- በሕይወትህ የአመራርን ጥበብ ካላዳበርክ የትም አትደርስም፡፡ ራስህን፣ ቤተሰብህን፣ ስራህንና ንግድህን ለመምራትም ሆነ ሕይወትህን በተዋቀረ መልክ ወደፊት ለማራመድ መሰረታዊ የአመራር ግንዛቤ ያስፈልግሃል፡፡ ይህ መጽሐፍ ከአመራር መሰረታዊ ትርጉም በመነሳት የተለያዩ የአመራር ጥበቦችን ማንም ሊገነዘበው በሚችለው መንገድ ያስተምርሃል፡፡



“25 የስኬት ቁልፎች”፡- ስኬትን የማይመኝ ሰው የለም፡፡ የስኬት ትርጉም ግን አወዛጋቢ የሆነበት ወቅት ላይ ነን ያለነው፡፡ ስኬት ለሚለው ቃል ሰዎች እንደ መነሻ ሃሳባቸውና እንደምኞታቸው ትርጉሙን ይለዋውጡታል፡፡ የስኬትን ትክክለኛ ትርጉምና 25 መሰረታዊ የስኬት ጎዳናዎችን ለመገንዘብ ይህ መጽሐፍ የግድ ነው፡፡ በ25 አስገራሚ ታሪኮች ላይ የተደገፈ አስገራሚ መጽሐፍ ነው፡፡



“የጊዜ አጠቃቀም ጥበብ”፡- ምንም ነገር ብትከስር መጨረሻ ላይ የምትከፍለው በጊዜህ ነው፡፡ የስልጣኔ ሁሉ ስልጣኔ ጊዜን በተገቢው መንገድ የመጠቀም ስልጣኔ ነው፡፡ በሕይወትህ እቅድ የሞላው ኑሮ ለመኖርም ሆነ ማንኛውንም ተግባርህን በወቅቱና በተዋጣለት ሁኔታ ለማከናወን ከፈለክ የጊዜ አጠቃቀምን መሰረታዊ እውነታዎች ከዚህ መጽሐፍ የማግኘት ምርጫ አለህ፡፡



“የስሜት ብልህነት”፡- በሕይወትህ ምንም አይነት የአእምሮ እውቀት ቢኖርህም በስሜት ብልህነትና ብቃት እስክትበስል ድረስ 80 በመቶውን የስኬት ምንጭ እንዳጣህ አትዘንጋ፡፡ የብዙ ስኬቶቻችን ምንጭ መነሻው ከጤናማ ስሜት ነው፡፡ የብዙ ውድቀታችን ምክንያትም ቢሆን መንስኤው ስሜትን በተገቢው ቦታ፣ መንገድና መጠን አለመግለጥ ነው፡፡ ይህንን ምስጢር በሚገባ ለማወቅ መጽሐፉ የግድ ነው፡፡



“እይታ”፡- ሁሉም ሰው ዛሬ የሚኖረው ኑሮ የሚወስንለት አመለካከቱ ነው፡፡ አመለካከታችን በዙሪያችን ካሉ ሰዎችና ከአካባቢያችን ጋር ያለንን ግንኙነት ይወስናል፡፡ አመለካከት በሂደት ወደ ተግባር የሚለወጥና በመጨረሻም ፍጻሜያችንን የሚነካ ጉዳይ ነው፡፡ መጽሐፉን በማንበብ አመለካከትህን ቀይርና ለሕይወትህ አዲስ መዓዛንና ጣእም ስጠው፡፡




“ትኩረት”፡- አንድን ነገር ጀምረን ብዙም ሳንራመድ ሌሎች ሃሳባችንን የሚሰርቁ ነገሮች ብቅ የሚሉበት ዘመን ውስጥ ነው ያለነው፡፡ የጀመሩትን ለመጨረስ፣ ውጤት ከሌላቸው ነገሮች ዘወር በማለት በዋናው ነገር ላይ ለማተኮርና ከአማካኝ ሰዎች ልቆ ለመገስገስ ትኩረት ወሳኝ ነው፤ በአጭር ጊዜ ብዙ ርቀት ለመሄድ ያስችላልና፡፡ይህ መጽሐፍ የትኩረትን ትርጉምና ተግባራዊነት በግልጽ ያሳያል፡፡



“የማንነትህ መለኪያ”፡- አንዳንድ ሰዎች የማንነታቸውን ዋጋ ካለፈው ታሪካቸው፣ ከወቅቱ ኑሯቸው፣ ሰዎች በእነሱ ላይ ካላቸው አመለካከትና ከመሳሰሉት ሁኔታዎች በመነሳት ይወስኑታል፡፡ የማንነታችን ዋጋ ግን ሊጨምርም ሆነ ሊቀንስ የማይችል ጉዳይ ነው፡፡ በማንነቴ ዋጋና በተለጠፈብኝ ተመን መካከል ልዩነት ሲኖር የማንነት ቀውስ ያስከትላል፡፡ ይህ መጽሐፍ በጉዳዩ ላይ ጥልቅ ግንዛቤን ያስጨብጣል፡፡



“ሁለንተናዊ ብልጽግና”፡- ብልጽግናን ከገንዘብ ጋር ብቻ አዛምዶ ማየት በሕብረተሰባችን መካከል የተለመደው ስህተት ነው፡፡ ብልጽግና ሁለንተናዊ ነው፡፡ ሁለንተናዊ የሆነን ብልጽግና ያላዳበረ ሰው በአንዱ ነገር በልጽጎ በሌላው ሊከስርና ቀድሞውን የበለጸገበትን ነገር ሁሉ ሊያጣ ይችላል፡፡ ስንት አይነት የብልጽግና ዘርፎች እንዳሉ ለመገንዘብና ያላቸውም ግንኙነት ለማወቅ ይህ መጽሐፍ ወሳኝ ነው፡፡



“የትራንስፎርሜሽን አመራር”፡- በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሁለት አይነት የአመራር ሂደቶች አሉ፡- ለውጥ-ተኮር (Transformational) እና ልውውጥ-ተኮር (Transactional)፡፡ የልውውጥ-ተኮር ስልት ጠቃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ዘላቂውና ውጤታማው አመራር ለውጥ-ተኮሩ ነው፡፡ ከግል ሕይወት አንስቶ እስከ ድርጅትና ማሕበራዊ አመራር የሚዘልቀውን የዚህን ስልት እውነታዎች የሚያስጨብጥ መጽሐፍ!



“የአለማችን አስቸጋሪ ሰዎች”፡- በሕይወትህ ከአስቸጋሪ ሰዎች በፍጹም ማምለጥ አትችልም፡፡ እኔና አንተም ብንሆን ለሌላው ሰው የሚያስቸግር ባህሪይ እንደሚኖረን አይካድም፡፡ ሰዎችን አያያዝ ሁኔታዊ ስለሆነ፣ እንዳለህ የቅርበት ሁኔታ ጥበብን ማዳበርን ይጠይቃል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በጣም የተለመዱ የአስቸጋሪ ሰዎች ባህሪይና እንዴት በጥበብ ልትይዛቸው እንደምትችል በሚገባ ትማራለህ፡፡



“ራስን ማሸነፍ”፡- ይህንና ያንን ለማሸነፍ ከመሞከራችን በፊት ማሸነፍ ያለብን ራሳችንን ነው፡፡ አለቀ! በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሁሉንም ነገር ለማሸነፍ የሚኖረን ጥረት የሚሰጠንን ጊዜያዊ ድል፣ በተቃራኒው ደግሞ ራሳችንን በማሸነፍ ዘላቂ ድል ውስጥ መግባት እንደምንችል ጥርት ባለ መልኩ እንማራለን፡፡ ከሁሉም በፊት ማሸነፍ ያለብን ችግራችንን ወይም ሰዎችን ሳይሆን ራሳችንን ነው!



“የገንዘብ ነጻነት አምዶች”፡- ማንኛውንም የሕይወትህን ሁኔታ የሚነካ መሰረታዊ ነገር ቢኖር ገንዘብ ነው፡፡ አሁን የምትኖረውን ኑሮ፣ የምትሰራውን ስራና የመሳሰሉትን ነገሮች የወሰነልህ የገንዘብ አቅምህ ነው፡፡ የገንዘብ ሁኔታህ ሲለወጥ ብዙ ነገር አብሮ ይለወጣል፡፡ ይህ መጽሐፍ ገንዘብን የማግኘት፣ የማባዛት፣ የመቆጠብና የመሳሰሉትን መሰረታዊና ወሳኝ ነገሮች ይነካል፡፡



“የሕይወት ጸጸት”፡- በሕይወትህ የምትደብቃቸው ነገሮችና የምትጸጸትባቸው ሁኔታዎች በበዙ ቁጥር የውስጥ ስቃይህ እየጨመረ እንደሚሄድ አትዘንጋ፡፡ ይህ መጽሐፍ የጸጸትን ትርጉም በትኖ ያሳይሃል፡፡ በየእድሜው የሚመጡ የጸጸት አይነቶችን ያብራራልሃል፡፡ ከጸጸት የመውጫውንም መንገድ ይጠቁምሃል፡፡ ከብዙ ሰዎችም የግል ልምምድ በመነሳት ተግባራዊ መመሪያዎችን ያካፍልሃል፡፡



“ገጸው ስሜት”፡- ብትወድም ባትወድም ስሜታዊ ፍጡር ነህ፡፡ ከፈቀድከለት ደግሞ ማንነትህን የመግዛት ፍላጎት ያለው አንድ ገጸ ስሜት አለ፡፡ ይህ ስሜት ፍርሃት ይባላል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የፍርሃትን ትክክለኛ ገጽታ በማየት የአሸናፊነትን ግንዛቤ ታገኛለህ፡፡ ይህንን አትዘንጋ፣ መፍራት እስከምታቆም ድረስ መኖር አልጀመርክም፡፡ መጽሐፉን አንብበውና በእውቀት ፍርሃትን አሸንፍ፡፡



“ምርጫና ውሳኔ”፡- የትናንት ምርጫህን ዛሬ እየኖርክ ነው፡፡ የዛሬ ምርጫህን ደግሞ ነገ ትኖረዋለህ፡፡ ሆኖም፣ አንዳንድ ጊዜ የሌሎች ምርጫዎች ወደ አንተ አልፈው የሚመጡበትም ጊዜ አለ፡፡ ለዚያም ቢሆን የምትሰጠውን ምላሽ የመለየትና የመምረጥ አቅሙ አለህ፡፡ ስለምርጫና ውሳኔ ትርጉም፣ ተጽእኖና ስለ ትክክለኛ ምርጫ ምስጢር ለመገንዘብ ወደ መጽሐፉ ጎራ በልና አንብበው፡፡



“ግንኙነትና አለመግባባትን መፍታት”፡- ሰዎች የምንናገረውንና የምንተገብረውን ነገር በእንዴት አይነት የተሳሳተ ሁኔታ እንደሚገነዘቡን ብናውቅ መናገርና ምንም ነገር ማድረግ እናቆማለን የሚባል አባባል አለ፡፡ ለማንኛውም ማሕበራዊ ሕይወት ጤንነት የትክክለኛ ግንኙነትን መመሪያዎች ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ በቃልና ቃል-አልባ በሆኑ መንገዶች ስለምናደርጋቸው ግንኙነቶች ትልቅ ሃሳብ ይዟል፡፡



“የጥበብ መንገድ”፡- እውቀት የተወሰነ መንገድ ይወስድሃል፣ ጥበብ ግን እስከወዲያኛው ያዘልቅሃል፡፡ አንዳንድ ሰዎች በብዙ እውቀት ተሞልተው እንኳን ብልሹ ሕይወት ሲኖሩ ማየት የተለመደ ነው፡፡ ይህ እንዳይሆን ከእውቀት የላቀውን የጥበብን መንገድ ማስተናገድ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ጥበብ ምን እንደሆነ፣ ከእውቀት በምን እንደሚለይና ጥበብን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ያመላክትሃል፡፡



“ሁለቱ ክህሎቶች”፡- ሁለት አይነት ክህሎቶች አሉ፡- አንደኛው የሞያ ክህሎት ሲሆን፣ ሌላኛው ግን ማሕበራዊ ክህሎት ነው፡፡ የመጀመሪያው ስራን በስኬታማነት እንድንሰራ ሲያደርገን፣ ሁለተኛው ግን ማሕበራዊ ግንኙታችን የሰመረ እንዲሆን ያግዘናል፡፡ ማንኛውም የሞያ ክህሎት ከማሕበራዊ ክህሎት ውጪ ብዙ ርቀት አያስኬደንም፡፡ ለማብራሪያውና ለግንዛቤው መጽሐፉን ማንበብ ጠቃሚ ነው፡፡



“አመኔታ”፡- አንዳንድ ሰዎች ሁሉንም ሰው በጭፍንነት የማመን ዝንባሌ ስላላቸው ሁል ጊዜ እየተንዱ ይኖራሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ማንንም ባለማመንና በጥርጣሬ ድንበራቸውን አጥረው ብቻቸውን ይንገላታሉ፡፡ ይህ መጽሐፍ ከጭፍን ጥርጣሬና ከጭፍን አመኔታ ጠርዞች ወጥተን ወደ ንቁ አመኔታ እንዴት ማደግ እንደምንችል በግልጽ ያሳያል፡፡ “እመን፣ ነገር ግን አጣራ!” የሚለውን እውነታ ተግባራዊ ያደርግልናል!



“የመገፋት ሕመም”፡- በራሳችን ላይ ባለን አመለካከትም ሆነ ከሌሎች ጋር በሚኖረንን ማሕበራዊ ግንኙነት ላይ ታላቅ ተጽእኖ ከሚያስከትሉ ልምምዶችና የስነ-ልቦና ቀውሶች መካከል የመገፋት ሁኔታ (Rejection) አንጋፋው ነው፡፡ የመገፋት ልምምድ ከማሕጸን ጀምሮ እስከ ሽምግልና እድሜያችን ድረስ ሲከተለን የሚኖር ሁኔታ በመሆኑ ስለጉዳዩ በቂ እውቀት ማዳበር ወሳኝ ነው፡፡



“የፍቅር ሕይወት”፡- ከምንለማመዳቸው የየእለት ስሜቶች መካከል የፍቅር ስሜት ጠንካራው ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በወጣትነት ጊዜ ራሳችንን ለትክክለኛ የፍቅር ሕይወት፣ አልፎም እስከመጨረሻው ለሚዘልቅ የትዳር ሕይወት እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል የሚጠቁሙንን ተግባራዊ ትምህርቶች ማንም ሰው በቀላሉ ሊገነዘበው በሚችለው መልኩ ተገልጸዋል፡፡



“ጀምሮ መጨረስ”፡- ሕይወት ጀምሮ የመጨረስ ሂደት ነች፡፡ የዚህች ሕይወት ጥራትና ስኬት የሚለካው ደግሞ በየጊዜው ጀምረን በብቃት በምንጨርሳቸው ነገሮች ነው፡፡ በትምህርት ዓለም፣ በፍቅርና በቤተሰብ ዓለም፣ በስራው ዓለምና በአጠቃላይ በራእያችንና በግቦቻችን ሂደት ውስጥ አንድን ነገር የመጀመር፣ የመቀጠልና በብቃት የመጨረስ ተግባራዊ መመሪያዎች ጥርት ባለ መልኩ ቀርበዋል፡፡



“የትዳር ሕይወት”፡- የተቃራኒ ጾታ ግንኙነት ከፍቅር ግንኙነትና ከእጮኝነት አልፎ ወደ ትዳር ሲዘልቅ ይዞት የሚመጣው ደስታና ፈተና በሚገባና በሚዛናዊነት ሊያዝ ይገባዋል፡፡ በሁሉም ነገር የተለያዩ ተቃራኒ ጾታዎች ወደ አንድነት ሲመጡ ይህንን፣ የ“አንድነት በሁለትነት” አዲስ ጎዳና በተሳካለት ሁኔታ የሚመሩበት መርሆች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በቀላሉ ሊተገበሩ በሚችል መልኩ ተብራርተዋል፡፡